# ምዕራፍ ሁለት

## የልመና ጥሪ ለእመቤታችን



**<u>እንደ መግቢያ</u>**

በምድር ያለው በሰማይ ካለው ጋር ቢቀራረብ በፍቅር፥
አይቶና ሰምቶ ዝም አይልም፥

ምላሽ ይኖረዋል ቸሩ እግዚአብሔር።
　　ይህ የልመና ጥሪ ነው - ለእመቤታችን፥
　　ስናስታውሳት በፍቅሯ ስበት ለምታባባን፥
　　ከሰማይ ሆና ለምታየን።
እንባ ሲንጠባጠብ - ሲነገር በስሜት፥
እንዲታወቅ በእውነት፤
የልመናው ብዛት - የጠብታው ብዛት፥
ይህ ልባዊ የጋራ ጸሎት፥
“እመቤታችን እባክሽ አማልጂን ከልጅሽ..” እያልን የምንጸልይበት፥
ይህ የልመና ጥሪ ነው - ለእመቤታችን፥
ከእኛ ከሰዎች ሁሉ፥
የኢትዮጵያን ደግ ደጉን ከምንመኝላት።

# የልመና ጥሪ ለእመቤታችን

ኢትዮጵያ - “ማርያም - ማርያም..” ብላ፥
ከምን ጊዜውም በበለጠ ጩኸት ጠራችሽ፤
ስቃይ ላይ ናቸውና የአስራት ልጆችሽ።
ኦ! ማርያም ወላዲተ አምላክ፥
ኦ! ቤዛይት አለም፥ የፍቅር እናት፥
ኢትዮጵያስ ካላንቺ  ማን አላት?
ማን አላት እንዳንቺ ደግ እናት።
　　የሥጋ ሞት እስኪለቀን፥
　　በቃችሁ እስኪለን፥
　　በጥዑም ዝማሬ እየቀደስን፥ እየዘመርን፥
　　“እሰይ ስለቴ ደረሰ - ለማርያምዬ ነግሬአት ነበረ..” እያልን፥
　　እየኖርን እንሞታለን፥ እየሞትንም እንኖራለን፤
　　ምንጊዜም ማርያም - ማርያም እንቺ አትጠፊምና ከሕይወታችን፤
　　አንረሳውምና ውለታሽን - ፍቅርሽን - ደግነትሽን - ተአምራትሽን።
ከአበቦች መካከል ጽጌረዳ፥
ከሴቶች መካከል - ምስለ ፍቁር ወልዳ፥
እባክሽ ተመልከች የልጆችሽን ፍዳ።

የማንነታችን ተምሳሌት - ማርያም እናታችን፥
እሜቤታችን ምነው ረሳሺን?
አትረሺንም፥ ይህንን እናውቃለን፤
ማን ለያይቶ ያገናዝባል? አንቺንና ኢትዮጵያን።
ብቻ የዘወትር ጸሎታችንን ለፈጣሪያችን እያቀረብን፥
አንቺንም እንማጸናለን፤
ከልጅሽ - ከወዳጅሽ እንድታማልጂን።
ልጅ ሲርበው እንደሚያስጨንቅ እናቱን፥
እኛም አንቺን መጮቅጨቅ ልማዳችን፥
ደጋግመን እንጠራሻለን፥ አንቀጸ ብርሃን፥
ኢትዮጵያን እልረሳሁአትም እንድትዪን፥
ተአምራትሺን እንድታሳዩን።
ምን እናድርግ?
ከላይ እስከታች፥ በጣረ ሞት ትግላችን፥
ግቢ ነፍስ፥ ውጪ ነፍስ ሆነብን፤
እባክሽ ፈጣሪያችንን ለምኚልን፤
ትንንቁን ወደ ሰላም እንዲቀይርልን፤
ከወደቀቺበት እንዲያነሳት ኢትዮጵያን፤
ሕዝቦች ናፍቀዋልና ለውጥን፥
ለድሆች የተመቸውን - መልካሙን።
በምድር ዙሪያ ከሁሉም አገር፥
እናውቃለን፤ ታያለሽ የሁሉንም ችግር፥
የእኛም ተስፋችን በጨለማ ዳመና ሲታጠር፥
ሞት እየገባ ከድሆቹ መንደር፤
ጭንቅና መከራ ስለበዛ በኢትዮጵያ ምድር፥
እዛኚቱ አድምጪን፤ ብሶታችንን ስንናገር።
ወንዝና ሸንጥሮ መረብ ሰርተው፥
ድንጋዩም አፈሩም ሳሩም ተመሳጥረው፥
ሜዳና ደኑ በየተራ ተሰልፈው፥
ከደጋው ሥፍራ እስከ ቆላው፥
ትዝ ይበልሽ አፍሪካ - ኢትዮጵያ፥ ከላይ እስከ ታች የቃኘሺው፤
ግን ያ መሬት ከልጅሽ ጋር ሆነሽ የባረክሺው፥
አሻፈረኝ ብሏልና፥

እስቲ እንደገና ጎብኘው።
ከምድር ብቅ ብሎ ከሚታይ ከፍታው፥
ዳሽን - የሰሜን ተራራ ከሚባለው፥
በደመና ከሚከናነበው፥
ሰማይ በፀበል ከሚረጨው፥
እስከ ቁልቁል እስከ ዝቅታው፥
ከገደሉ ሥር ከረባድው፥
እስከ ዱብቲ - ዳሎል አሳይታ ንዳድ ከሚያጠቃው፥
ከላይ ባህረ ኤርትራን ተከትሎ፥
ቁልቁል በኤደን ሰላጤ በተከፈለው።
በመሃል የስምጥ ሸለቆ የሚሰነጥቃት፥
በግራና በቀኝ፥ ተራሮች በሰንሰለት የተሳሰሩባት፥
እንዲህ ከፍታና ዝቅታ የበዛባት።
የኢትዮጵያ ምድር - ለልጅሽ የሚሆን ገጸ-በረከት፥
ወርቅ፥ እጣንና ከርቤ የተገኘባት...............፤
ኢትዮጵያ፥ የልጆችሽ መኖሪያ፥
ከዚህም ከዚያም ምድጃና ጣርያ፥
የሰውም የአውሬውም መሸሸጊያ፥ መጠለያ፥
መፈጠሪያ፥ መኖሪያ፥ መሞቺያና መቀበርያ።
እናታችን ማርያም፥ እባክሽ ስሚን፥
በጣር ላይ ቆይታለች እኮ አገራችን።
ከተፈጥሮም ይሁን ከሰው፥
አየሩ ተለውጦ፥
ዝናብ ጠፍቶ፥ ዳመናም ከሰማዮ ተሟጦ፥
ወንዙ ደረቀ፤
የተዘራውም በጸሐይ ሙቀት ተቃጠለ፤
የደረቀው መሬት፥
ለሰውም ለእንስሳም አልሆነለት፤
የሚበላ የሚቀመስ ጠፍቷልና ለዓመታት።
ምድሪቱ ከተፈጠረች ጀምሮ፥
የስበቶች መደነቃቀፍ እንዳይፈጠር፥
የአንዱ አካል ስበት ወደሌላው ተዛምቶ፥
የጠፈር አካላትን ዙረት በያሉበት አቆይቶ፥

ምድሪቱ የጸሐይ ሙቀትና ብርሃን አጥታ ሳትቀዘቅዝ - ሳትጨልም፥
ሁሉን አስተካክሎ ለዘማናት ያቆየ አምላካችን፥
ኢትዮጵያን ተቆጥቶ ሊቀጣት ይሆን?..
የሰው ልጅ የገዛ ሥራው እንዲያስለቅሰው፥
ይህ ከሆነ ተፈጥሮአዊ ሕግ የተደነገገው፥
ይበለው! ይበለው! ነው የሚባለው?
አዬ! ምንም ይሁን ምን -
ብቻ በቃችሁ እንዲለን ለምኚልን፥
ሃዘን በዝቷልና ባለማችን - ባገራችን፥
እባክሽ ማርያም ይህንን ልመና አሳርጊልን።
ስምሽን ስንጠራው ስንለምንሽ፥
ማርያም አስታውሺን በልብሽ።
ከዚህም ከዚያም ኃጢአት ይሠራል፤
ቸሩ ፈጣሪያችን የሰውን ድካሙን ያውቃል።
ከአበቦች መካከል ጽጌረዳ፥
ከሴቶች መካከል - ምስለ ፍቁር ወልዳ፥
እባክሽ ተመልከች የልጆችሽን ፍዳ።
በዚያች ሥፍራ - በጥንታዊት፥
ምድራዊያን ነፍሳት እንዳልፈነጩባት፥
አሁን ፍጥረታት ረገፉባት።
በዚች ሥፍራ - ዘመናዊት፥
ስንድህ፥ ስንሮጥ፥ ስንጫወት፥
በፍቅርና በደስታ እንዳላደግንባት፥
ዛሬ ትለውጣ፥
የሃዘን ቤት ሆና አየናት፤
ሰው እንደ እንጨት ሲነድባት፥
እንደ ከሰልም ሲከስልባት፥
ምድሪቱን ረሃብ ሲረጋግጣት፥
ቋሚው ሲደፋባት፥
ሙታን ሲራባረቡባት፥
አዬ! ምነው እመ ብርሃን?
ምነው ቸላ አልሻት ኢትዮጵያን፥
ምነው የማትሰሚያት - ጩኸቷን ልቅሶዋን?

ሰቀቀኗን - ሰቆቃዋን - የሞት ሽረት ጣሯን።
ውሃ ባይጣፍጥ አይመር፥
መጥፋቱ ነው እንጂ የሚያሳርር።
የመብዛቱን ያህል ሕይወት ጠፍቶ፥
መንግሥትም ድሆች በረሃብ ሲነደፉ - አይቶ - ከፍቶ፥
ማድረግ የሚቻለውን ሳያደርግ ቀርቶ፥
ሁሉም ነገር ከሰው አቅም በላይ ሲመስል፥
ሰማይ ከምድር የመራቁን ያህል፥
የአምላክ ምሕረቱ ርቆብን ስንማልል፥
እባክሽ ስሚን ስንጮህ - “ድረሺልን! ድረሺልን!.....” ስንል።
ከአበቦች መካከል ጽጌረዳ፥
ከሴቶች መካከል - ምስለ ፍቁር ወልዳ፥
እባክሽ ተመልከች የልጆችሽን ፍዳ።
ኢትዮጵያ - ማርያም ማርያም ብላ አንቺኑ ጠራችሽ፤
ስቃይ ላይ ናቸውና ልጆችሽ።
እባክሽ የሰላሙን በር ክፈቺላት፤
በደጇ ወጥቶ ይቅር፥
አይመለስ ጠላትነት፤
ክፋት ይጥፋ ዘረኛነት።
እባክሽ የፍቅርን በር ክፈቺላት፤
ሕዝቦች ናፍቀዋልና እድገት፥
ኑሮ - በእኩልነትና በአንድነት።
እኛ ብንጮህ፡- ኢትዮጵያ - ኢትዮጵያ እያልን፥
ብንማጸን መሬቱን - አፈር ድንጋዩን፥
ምንድነው ትርፋችን?
ጊዜና ለውጥ ሁሉን አሳይቶን፥
ሥጋ ካለመንፈስ ባዶ መሆኑን አስተምሮን፥
በሚገባን ቁኣንቁኣ ተአምረ ማርያም ተነቦልን፥
እኛም ሰምተን፥ ቁንቁኣችንን አሳደገልን፤
እናትነትን ከፍቅር ጋር አሳየን፤
ሁለቱን ነጣጥሎ ማያት እስኪያቅተን።
ታዲያ እንዴት ብለን እናያለን ራሳችንን?
ሕይወታችንን ካንቺ ነጥለን።

ለዚህ ነው ጸሎታችን፥
መንፈስ አልባ እንዳይሆን ሕይወታችን፥
በረከት እንዳያጣ ምድራችን።
ከአበቦች መካከል ጽጌረዳ፥
ከሴቶች መካከል - ምስለ ፍቁር ወልዳ፥
እባክሽ ተመልከች የልጆችሽን ፍዳ።
ካንቺ የተወለደው - አልበቃ ብሎት መዳናችን፥
ከመስቀሉ ላይ ሆኖ፥ ፊቱን ዘቅዘቅ አድርጎ፥
አንቺን አየሽ ልጅሽ፥
አልተለወጥሺም አንቺ ያው አንቺ ነሽ፥
ለልጅሽ እናት እንደሆንሽ፥
ለአለም ሕዝብ ሁሉ እናት የመሆን ብቃት ያለሽ።
እንደገናም ከመስቀሉ ላይ ሆኖ፥ ፊቱን ዘቅዘቅ አድርጎ፥
ዮሓንስን ተመለከተ የሚወደውን፥
እንዲሁም አሰበ የምድሪቱን ክፋቷን፥
ጠባቂ እናት ማስፈለጉን።
አንቺን እና ዮሐንስን እናትና ልጅ ያደረገ አምላካችን፥
ያውቃልና ለሚያፈቅር ልጅ የእናት ፍቅር ማስፈለጉን፥
ጌታ ኢየሱስ አንቺን ሰጠን፥
“እንኩ ውሰዷት፥ እናት ትሁናችሁ” አለን፥
ይወዳቸዋልና ወዳጆቹን - ቤተሰቡን፤
በመስቀል ላይ ሆኖ አይቷልና የምድሪቱን - ስቃዩአን፤
ያውቃልና ማስፈለጉን - የፍቅር እናት ለኢትዮጵያችን፥
የመዳናችን ምልክት ማርያም ጽዮን፥
አገራችን፥ ከተማችን፥ ታቦታችን፥
የተስፋችን ነጸብራቅ፥ ቃል ኪዳን፥
የሰላማችን ምልክት፥ ቀስተዳመና - ባንዲራችን፥
የኖህ መርከብ - ሰማያዊ ቤት - እናታችን፥
ቅድስት ማርያም ልጅሽ አንቺን ለኛ ሰጠን።
ታዲያ፥ ማርያም፥ አንቺን ትተን የት እንደርሳለን?
አምላካችንን ስንጠራ በዘውትር ፀሎታችን፥
ስላመንብሽ እኮ ነው! አማልጂን ማለታችን።
ከጣና ደሴቶች፥ ከባህር ዳር፥

ከሸዋ፥ ከወለጋ፥ ከሲዳማ እስከ ሐረር፥
ከአስመራና እና ከአክሱም፥
ማን አለ? ያላጌጠ ባንቺ ስም።
ከደቡብ ከሻሸመኔ፥ ከመሃል ከደብረ ብርሃን፥
ከዚያም አልፎ እስከ ሰሜን፥
ማርያም ተስለሻል ባይምሮአችን፤
ምንጊዜም አንረሳም አንቺን።
በኢትዮጵያችን ሰው ቢወለድ፥ ቢሞት፥
አልተለመደም ባይተዋር ሕይወት፥
ማርያም ማርያም የማይባልበት።
ማርያምን ሳይዙ ጎዞ፥
ኢትዮጵያ አልለመደባትም፤
ተዘፈነ፥ ተዘመረም፥ ተለቀሰም፥
ማርያም አልባ ስሜት አይታወቅም።
የኢትዮጵያ ሕዝቦቿ ቢለያዩም እንደየመኖሪያቸው፥
ካንቺው ጋር ነው አንድነታቸው፥
መንፈሳዊው ልቦናቸው።
በስደት አለም የአገር፥ የወገን፥ የዘመድ ሃሳብ፥
ናፍቆቱም ሲከብዳቸው፥
ለትልቁም ለትንሹም - “እናቴ ባየሺኝ፥...”
“ማርያም - ማርያም...” ማለት ልማዳቸው።
አንዳንዶችም በንስሃ ራሳቸውን እስኪያስተካክሉ?...
ሁሉም እንደየቅሉ፥
አምላካቸውን ሲለምኑ ፈራ ተባ እያሉ??...
ግን መፍትሔ እስኪያገኙ እየተቻኮሉ፤
ማርያም አንቺን ሲለምኑ ሙጭጭ ይላሉ።
ታዲያ ምንድነው ጥፋቱ አንቺን መቅረቡ?
ምድራዊነት ሲያስጨንቀን አይኖቻችን ሲያነቡ፥
የልጅሽን ስጦታ መናቅ ነውና አንቺን መርሳት፥
አይሰለቸንም፥ ያንቺንም ስም መጥራት፤
አዎን! ስምሽን እንጠራለን - ባንቺ አናፍርም፤
የአምላካችን ውለታ ምንጊዜም አይረሳም።
አሁንም - ነይ ነይ እንልሻለን እምዬ ማርያም፥

ቤዛዊት አለም፥............
ትንፋሻችን - ተስፋችን ነሽና ለዘለአለም።
ከአበቦች መካከል ጽጌረዳ፥
ከሴቶች መካከል - ምስለ ፍቁር ወልዳ፥
እባክሽ ተመልከች የልጆችሽን ፍዳ።
አዬ! ምነው! እመ ብርሃን? ኢትዮጵያን ጨከንሽባት?
ክፋትና ጭካኔ ሲከባት፥
ችጋር ሲዘምትባት፥ ስቃይ ሲጠናወታት።
ማርያም ወዳንቺ ነውና መዝሙራችን፥
በሃዘናችን ፈጥነሽ ድረሺልን፥
ብሷልና ብሶታችን፤
እባክሽ እንባችንን በእጆችሽ አብሺልን።
ናስተማስለኪ ብለው ሊቃውንቱ፥
ድብቅ እውነቶችን ሲጎትቱ፥
ጉልህና የሚታየውን ከረቂቁና ከማይታየው እያዛመዱ፥
በመንፈስም አርቅቀው እየሄዱ።
መንፈሳዊ ክስተቶችን በገሃድ ሲያሳውቁ፥
ምስጢራትን ከጥልቁ እየጠለቁ።
ታዲያ ዝም ማለትን ማን ችሎ፥ ማን ይናገር?
ከመሃይሙም ሲወጣ የማርያም ነገር፥
ሲገለጥ የተምሳሌቱ ምሥጢር።
በደብረሲና ከቁጥቋጦው መሃል፥
እሳት ሆኖ ቅጠል እንደማያቃጥል፥
ያ እሳት - ያ የእግዚአብሔር ቃል፥
ባንቺ ሲያድር ማሕጸንሽን ሳያቃጥል፥
እመቤቴ ያንቺማ ነገር መች ተነግሮ ያልቃል?
ስምሽን ገና ከማሕጸን ስንወጣ ሰምተነዋል፤
በመንፈስ እናትነትሽንም አውቀነዋል፥
በጥልቀቱ የማያስብ፥ የማይመራመር፥
አይገባውም ያንቺ ነገር።
ሰማይማ ሳይኖር መሬት እንዴት?
እናትማ ሳትኖር ልጆች እንዴት?
ታዲያ ምነው አዛኚቱ? እንዴት- እንዴት፥

ኸረ! ምነው - ምነው! እመ ብርሃን?
በኢትዮጵያችን የቁም ስቃይ ሲበዛባት፥ የምድር ችጋር ሲዘምትባት፥
ምነው ማርያምዬ - ስቃይ ፈተናዋን፣ ይበቃል የማትያት?
ልጆችሽ እምዬ - እምይዬ እያሉ ሲጮሁ በአንድነት፥
በእውነት አንቺም ችለሽ መቀነትሽን ታጠብቂባት?
ምድሪቱ ዋይ ዋይ እያለች ትጮሃለች፤
ማርያም እመቤቴ ድረሺልኝ እያለች።
ዛሬም ነገም የኛው - ለኛው የተሰጠሽ፥
እምዬ ማርያም አንዴት አስችሎሽ ዝም አልሽ?
ዝም ማለትን ችሎ፥ ማን ዝም ይበልልሽ?
ከዘመነ ፍዳ ወደ ዘመነ ምህረት ስንሸጋገርብሽ፥
አንቺው ጽላተ ሙሴ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ማደሪያ ሆነሽ፥
የአምላክ እናቱ ለመሆን በመብቃትሽ፥
እኛም ልጆችሽ አፈቀርንሽ፥
ትውልድ ሁሉ ብፅእት አለሽ።
የትህትና፥ የደግነት ተምሳሌት - ክብራችንም በመሆንሽ፤
እናቶች፥ አባቶች፥ ልጆች ሁሉ የሰገዱልሽ፥
ማርያም አንቺ በእውነት የጠፈር ንግሥት ነሽ።
ታዲያ፥ አንቺ ርህሩህ እናት ሆነሽ፥
የጭንቃችንን ሸክም እያየሽ፤
እንዴት ልብሽ ችሎ ነው እንዲህ የዘገየሽ?
ምን ይሆን ምክንያቱ፥
ችግሮቻችንን ለፈጣሪ ያላቀረብሽ?
እንዳመንብሽ አትርሺን እባክሽ።
ከአበቦች መካከል ጽጌረዳ፥
ከሴቶች መካከል - ምስለ ፍቁር ወልዳ፥
እባክሽ ተመልከች የልጆችሽን ፍዳ።
እናውቃለን - ከችግራችን አንጻር ልመናችን ሰሚ አለው፤
እርሱ ፈጣሪያችን ነው፥
ችግሮቻችንን ሁሉ የሚያጠፋው፤
ከእለት ህኪትም የሚያድነው።
እውቀትና ችሎታ በማይወስነው፥
ማቅ ለብሰን፥ ተደፍተን ነው የምናለቅሰው።

ስለዚህ እባክሽ በርትተሽ ልጅሽን ለምኚልን፡-
“ልጆቼ ጭንቅና መከራው ይብቃቸው፤
ወዳጆቼን ከችግር አውጣልኝ” በዪው።
እኛም በጸሎት እንበረታልን፤
እመቤታችን - እናታችን አማልጂን፤
ጸሎታችንን ወደ ሰማይ አሳርጊልን።
አሜን።

<u>*መዝሙር*</u>

ለአገር ወገን ሳስብ፥
ትዝ ትለኛለች ማርያም፤
እርሷም ልጆቿን አትረሳም፤
ዝም ብላ ዝም አትልም። (2 ጊዜ)

ይድረስ የልመናዬ ጥሪ ለእመቤቴ፥
እርሷ ናትና ደጉኣ እናቴ፥
ማርያም ማርያም ይላል አንደበቴ፥
ጭንቀቴ ግፍፍ ይላል ከአከላቴ፤
ምግብ ቢጠፉ፥ ሰውም ቢጠፉ፥
ከእመቢቴ አገኛለሁ ልዩ ተስፋ።
እርሷን ይዤ አልጎዳም፥
ክፉ መንፈስ አይነጥቀኝም።

ለአገር ወገን ሳስብ፥
ትዝ ትለኛለች ማርያም፤
እርሷም ልጆቿን አትረሳም፤
ዝም ብላ ዝም አትልም። (2 ጊዜ)

ስቃይ ቢበዛብን - ሃዘን ቢውጠን፥
የእግዚአብሔር ኃይል ካለ - ምንም አንሆን፤
ለሌላው እናስብ፥ ከራሳችን አልፈን፤
በሕብረት ስንጸና ፈጣሪም አይረሳን።

የዘወትር ጸሎት እናድርስ ሁላችን፤
ለአገር ለወገን ይሁን ልመናችን።
ሃዘነ ልቦናን የምታቀልልን፥
ደጊቷ እናታችን አለች ከጎናችን።

ለአገር ወገን ሳስብ፥
ትዝ ትለኛለች ማርያም፤
እርሷም ልጆቿን አትረሳም፤
ዝም ብላ ዝም አትልም። (2 ጊዜ)